የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፸፩
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20[th] Year No.71
ADDIS ABABA 4[th] September, 2014

## ማውጫ

## CONTENTS

ደንብ ቁጥር ፫፻፲፮/፪ሺ፮ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……ገጽ ፯ሺ፮፻፲፯

Regulation No. 316/2014

Ethiopian Water Works Construction Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation………………Page 7617

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፲፮/፪ሺ፮**

**የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) (ሀ) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፲፮/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 316/2014**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN WATER WORKS CONSTRUCTION ENTERPRISE**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Water Works Construction Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 316/2014".

2. **Establishment**

1/ The Ethiopian Water Works Construction Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

www.chilot.me

**፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የውሃ፣ የመስኖና የኢነርጂ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት**

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፭. ዓላማ**

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ የውሃ ሀብትን ለማልማት የሚሠሩ የግድብ ሥራዎችን፣ የመስኖ ሥራዎችን፣ የውሃ ኃይል ማመንጫ ግንባታዎችን፣ የውሃ ማከፋፈያ መስመሮች ሥራዎችን፣ የቆሻሻ ማስወገጃ መስመሮች ሥራዎችን፣ የድሬኔጅ ሥራዎችን፣ የጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ሥራዎች፣ የሪክላይ ሜሽን ግንባታዎችን፣ የወንዝ መቀልበስ ግንባታዎችን እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመንገዶችና የሕንፃ ግንባታዎችን ማከናወን፣

፪/ በፌደራል መንግሥት ወጪ የተገነቡና የሚገነቡ የመስኖ ግድቦችን በባለቤትነት ማስተዳደር፣ ከተጠቃሚዎች የሚሰበሰበውን ገንዘብ ለተመሳሳይ ግድብ ሥራ ማዋል፣

፫/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፣

፬/ ለሥራው የሚያስፈልጉትን የተለያዩ ቧንቧዎችን ማምረትና እንደ አግባብነቱም መሸጥ፣

፭/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት፡፡

**፮. ካፒታል**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፲፮ ቢሊዮን (አሥራ ስድስት ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፬ ቢሊዮን ፮፻፳፱ ሚሊዮን (አራት ቢሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

3, **Supervising Authority**

The Ministry of Water, Irrigation and Energy shall be the supervising authority of the Enterprise.

4. **Head Office**

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch office elsewhere as may be necessary.

5. **Objective**

The objectives for which the Enterprise is established are:

1/ to engage in the construction of water works relating to dams, irrigations, hydropower generations, water supply systems, sewerage systems, drainages, deep water wells, reclamations, river diversions and, as may be necessary, in the construction of roads and buildings;

2/ to own and administer irrigation dams constructed and to be constructed by finance of the federal government and re-invest the proceeds of charges collected from the beneficiaries of such dams for the construction of other similar dams;

3/ in line with the directive and policy guideline issued by the Ministry of Finance and Economic Development, to sell and pledge bonds and to negotiate and sign loan agreement with local and international financial sources;

4/ to manufacture different kind of pipes necessary for its activity and sell as may be appropriate;

5/ to engage in other related activities necessary for the attainment of its purposes.

6. **Capital**

The authorized capital of the Enterprise is Birr 16,000,000,000 (Sixteen Billion Birr) of which Birr 4,629,000,000 (Four Billion Six Hundred Twenty Nine Million Birr) is paid up in cash and in kind.

www.chilot.me

**፯. ኃላፊነት**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

**፰. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**፱. የተሻረ ደንብ**

የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፮/፲፱፻፹፮ (እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**፲. የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፮/፲፱፻፹፮ (እንደተሻሻለ) ተቋቁሞ የነበረው የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

**፲፩.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**7. Liability**

The Enterprise may not be held liable beyond its total assets.

**8. Duration**

The Enterprise is established for an indefinite duration.

**9. Repealed Regulation**

The Water Works Construction Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 156/1993 (as amended) is hereby repealed.

**10. Transfer of Rights and Obligations**

The rights and obligations of the Water Works Construction Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No.156/1993 (as amended) are hereby transferred to the Enterprise.

**11.Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 4th day of September, 2014.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me